# Learning by Ear 2013

**"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 2: «**ያልተለመዱ ሀሳቦች** »

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: አቶ ሙላቱ IN THE CELL AT THE POLICE STATION**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ፖሊስ ሙሉጌታ(M, 40)**
- **SUSPECT 1 (M, ADULT)**
- **SUSPECT 2 (M, ADULT)**
- **3 OTHER INMATES (M, ADULTS)**

**SCENE 2: ምኞቱ ASKS ትዕግስት TO MOVE IN**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ምኞቱ (M, 35)**

**SCENE 3: AT THE POLICE STATION**

- **ፖሊስ ሙሉጌታ(M, 40)**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **OFFICER 2 (M, 30’S)**

**SCENE 4: አቶ ሙላቱ’S FAMILY IN TANDIKA SLUMS**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (M, 40)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**

## INTRO

### 1. NARRATOR:

ጤናይስጥልን በድጋሚ። ይህ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ በሚል ርዕስ የሚቀርበው የሬዲዮ ድራማ ነው። ወጣት አፍሪቃውያን እና ቤተሰቦቻቸው የሚገጥሟቸውን ፈተናዎች ሰምተናል። ቀደም ሲል የ15 አመቷ ምህረት ሙላቱ ማርገዟን ተገንዝባለች። ጓደኛዋ ትዕግስት ደግሞ በግልፅ መፍትሄ ይሆናል ብላ የምታስበውን ነግራታለች:

### 2. EPISODE 1, LINES 8 – 11:

*ትዕግስት (8): ምህረት፤ እስቲ ተረጋጊ። ቀደም ብዬም ነግሬሻለሁ። ቀላል መፍትሄ* አለው።*(…)*

*ምህረት (11):* ትዕግስት ነገሩ አልተመቸኝም … ምን መሰለሽ። በዛ ላይ ዶ/ር ዘሪውንን የምከፍለው ገንዘብ ከየት አገኛለሁ?

## 3. NARRATOR:

**የምህረት ታናሽ ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ ደግሞ መጥፎ ነገር  ሳያጋጥማቸው ከማይቀርበት ጎረቤት ሀገር ላቦሪያ ተመልሰዋል። :**

***KW BEGIN***

## 4. EPISODE 1, LINES 92 – 94:

***ቅዱስ: ክፉ ነሀ ብሩክ። ልክ ላቦሪያ ማዕድን ማውጫ እንዳሉት ልጆች።***

***ብሩክ: ቅዱስ፤ ስለ ማዕድን ማውጫው ለማንም መንገር የለብንም። ይህንን ነው አክስት ለምለም እና አቶ ካሳሁን የነገሩን።***

***KW END***

## 5. NARRATOR:

**ይህ በእንዲህ እንዳለ አባታቸው አቶ ሙላቱ አሁንም ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደተያዙ ነው። የምህረት የክፍል ጓደኛ የሆነውን የንጉሴን ሀብታም ቤተሰብ ንብረት በመዝረፍ አሁንም ይጠረጠራሉ። በዛሬው «ያልተለመዱ ሀሳቦች » በተሰኘው ጭውውት አቶ ሙላቱ በእስር ቤት ከፍርግርግ ብረቶቹ ጀርባ ሳሉ እንጎበኛቸዋለን።**

## <u>SCENE 1: አቶ ሙላቱ IN THE CELL AT THE POLICE STATION</u>

## 6. ATMO: INSIDE THE CELL AT POLICE STATION

## 7. INMATES CHATTING IN THE BACKGROUND

8. **SUSPECT 1:** እሺ ሙላቱ « አቶ አደገኛው ወንጀለኛ» ምን አድርገህ ነው ከኛ ጋ የተቀላቀልከው?

9. **አቶ ሙላቱ:** እኔ እንደናንተአይነት አይደለሁም። እንደውም እኔ ህግ አስከባሪ ነኝ።

***KW BEGIN***

10. **SUSPECT 1:** **(sarcastic)** ኦኦ! ፖሊሱ ከኛ ጋ አንድ ክፍል እየተጋራ ነው?

11. **SUSPECT 2:** **(laughs sarcastically)** አቶ ሙላቱ ፖሊስ አይደለም። ዘቡሌ ነው። የዛን ሀብታም ጃለታ ቤት ሲጠብቅ ነበር።

12. **SUSPECT 1:** አየህ! እዚህ እኛ ዘበኞቹቹ አንተ ደግሞ ዝም ብሎ ተራ ሰው ነህ።

***KW END***

13. **SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS THEY GRAB** አቶ ሙላቱ

14. **SUSPECT 1:** ና! ወዲህ። የታል ገንዘቡ?

15. **አቶ ሙላቱ:** **(scared)** የምን ገንዘብ?

16. **SUSPECT 2:** ከጃለታ የሰረቅከው ገንዘብ ነዋ። የማናውቅ መሰለህ? **(to other suspect)** ኪሱን ፈትሸው!

17. **SFX: CLOTHES RIPPED**

18. **አቶ ሙላቱ:** ስማ! ሰውዬ ዞር በል ወደዛ እጆችህን ከላዬ ላይ አንሳ!

19. **SFX: HEAVY STEPS APPROACHING**

**20. SFX: RAP ON METAL WITH BATON**

**21.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ምንድን ነው ይሄ ሁላ ጫጫታ ? ምን ነው እዚህ እስር ቤት ውስጥ እየሆነ ያለው?

**22. SILENCE**

**23. SFX: CELL DOOR UNLOCKED, OPENS**

**24.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ተጠርጣሪ ሙላቱ ወዲህ ይውጡ!

**25. SFX: FOOTSTEPS** አቶ ሙላቱ

**26. SUSPECT 1: (low voice)** በእዚሁ ያመለጥሽ እንዳይመስልሽ። ስትመለሺ እናገኝሻለን።

**27. SFX: CELL DOOR SHUT AND LOCKED**

**28. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: ምኞቴ ASKS ትዕግስት TO MOVE IN</u>**

**29. ATMO: BUSY STREET, TRAFFIC**

**30. SFX: FOOTSTEPS OF 2 GIRLS WALKING ON THE STREET**

**31.** ትዕግስት: ውይ! ኡፍ የዛሬውስ ትምህርት በእዚሁ አለቀ!

**SILENCE**

**32.** ትዕግስት: እንዴ ምህረት?

**33.** ምህረት: **(lost in thought)** ንገሪኝ ትዕግስት፤ በጣም ያማል?

**34.** ትዕግስት: ምኑ ነው የሚያመው ምህረት?

**35.** ምህረት: ሂደቱ ነዋ! ከዚህ ቀደም አድርጌ አውቃለሁ አላልሽም።

**36.** ትዕግስት: ውይ ፅንስ ማስወረዱን ማለትሽ ነው? ብታይ ምንም --

**37. SFX: FOOTSTEPS APPROACH**

**38.** ምኞቴ: **(suddenly)** አሀሳ፤ ታድያስ እንዴት ናቹህ?

**39.** ትዕግስት: **(startled)** ውይ! እንዲህማ አታስደንግጠን ምኞቴ!

**40.** ምኞቴ: **(laughs)** ይቅርታ። አምጪ ደብተርሽን ላግዝሽ ትዕግስት!

**41.** ትዕግስት: **(Unfriendly)** ራሴው መያዝ እችላለሁ።

**42.** ምኞቴ: ዋ! የኔ ትዕዛዝ ነው።

**43. SFX: THEY FIGHT ABOUT THE BOOKS**

**44.** ትዕግስት: ባክህ አቁም!

**45. SFX: BOOKS AND PAPERS FALL**

**46.** ትዕግስት: **(angry)** የምትሰራውን ተመልከት። ደብተሮቼን በሙሉ መሬት ላይ ዘረከፍካቸው። ይህንን ነው ርዳታ የምትለው?

**47. SFX: RUSTLING,** ትዕግስት **PICKING UP BOOKS RAPIDLY**

**48.** ምኞቴ: አዝናለሁ። (to ምህረት) ይቅርታ ምህረት አንዴ ከትዕግስት ጋ ብቻችንን ትተይን?

**49.** ምህረት: ምንም ችግር የለም።

**50. SFX: FOOTSTEPS ምህረት LEAVES**

**51.** ምኞቴ: የኔ ቆንጆ ትዕግስትዬ፤ ምንድን ነው እንደዚህ ያናደደሽ?

***KW BEGIN***

**52.** ትዕግስት: ከእንግዲህ ያንተ ትዕግስት አይደለሁም። ከሌሎች ሴቶች ጋ አብረህ እየተኛህ ተላላፊ የአባላጠር በሽታ አስይዘህኛል! በዛ ላይ ደውለህ እንኳን እንዴት ነሽ ልትለኝ አልፈለክም። አንተማ የኔ ነገር በቃ ምን ያስጨንቅሃል

**53.** ምኞቴ: ተይ እንጂ ትዕግስትትዕግስት ፤ እንዴ! አንቺ ራስሽ ከስንቱ ልጆች ጋ ተኝተሻል።

***KW END***

**54.** ትዕግስት: ጊዜዬን እያቃጠልክ ነው ምኞቴ። በኔ በኩል ጨርሻለሁ።

**55.** ምኞቴ: (convincing) በጣም ነው የናፈቅሽኝ። ተመልሰን አብረን እንድንሆን እፈልጋለሁ ተመልከች- ያመጣሁልሽን።

**56. SFX: BANK NOTES BEING COUNTED**

**57.** ትዕግስት: ምንድን ነው?

**58.** ምኞቴ: የፈለግሽውን ነገር እንድትገዢ የተወሰነ ገንዘብ ይኸውልሽ፤ ልክ እንደድሮዋችን …በይ ተቀበይኛ!

**59.** ትዕግስት: ከእንግዲህ ያንተን ገንዘብ አልፈልግም።

**60.** ምኞቴ: እባክሽን ትዕግስት። ተቀይሬያለሁ። ይህንንም ላረጋግጥልሽ እፈልጋለሁ። በቃ ከአሁን በኋላ አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ?

**61. SFX: BOOKS FALLING DOWN AGAIN**

**62.** ትዕግስት: **(surprised)** ምን?

**63.** ምኞቴ: **(convincing)** አፈቅርሻለሁ ትዕግስት።

**64.** ትዕግስት: **(confused)** ምኞቴ… እኔ… እኔ አላውቅም።

***KW BEGIN***

**65.** ምኞቴ: በእውነት ነው የምልሽ ተቀይሬያለሁ። ህይወቴን በሙሉ አብሬያት ለማሳለፍ የምፈልጋት ሴት ብትኖር አንቺ ነሽ።

**66.** ትዕግስት: **(unsure)** እንዳገባሀ ነው እንዴ እየጠየከኝ ያለኸው? እንዴ ቆይ ለወላጆቼስ ምን  ልላቸው ነው? ደግሞ የትምህርቴስ ነገር?

**67.** ምኞቴ: እናትሽ ቅር የሚላቸው አይመስለኝም፤ አባትሽ ደግሞ እቤት ከሚኖሩበት የማይኖሩበት እንደሚበልጥ ነግረሽኛል!

**68. ትዕግስት:** ግን እኮ ለትምህርት ቤት እና ለቤት ኪራይ የሚከፍልልን እሱ ነው። እማዬ ለአንድ ወይንም ለሁለት ሌሊት ከቤት ወጥቼ ብቆይ ምንም አትልም። ግን ከአንድ ወንድ ጋ አብሮ ለመኖር...

**69. ምኞቴ:** እረ ባክሽ ይኼን ያህል አታካብጂ። እኔ ጋ ስትሆኚ እኮ ወደ ትምህርት ቤት አትሄጂም ያለ የለም። እና ደግሞ የሚያስፈልግሽን ነገር በሙሉ አሟላልሻለሁ።

**70. ትዕግስት:** ምኞቴ ቢሆን ደስ ይለኛል ግን...

**71. ምኞቴ:** ግን ምን ትዕግስት?

***KW END***

**72. ትዕግስት:** ቆይ ትንሽ ላስብበት።

**73. ምኞቴ:** እሺ ግን እድሜ ልክ አልጠብቅሽም።

**74. SFX: STEPS - ምኞቴ LEAVES**

**75. ትዕግስት:** **(sighs)**

***KW BEGIN***

**76. SFX: STEPS ምህረት APPROACH**

**77. ምህረት:** እንዴ ትዕግስት ይኼን ያህል ጊዜ ምን ነው? ደብተሮችሽ አሁንም መሬት ላይ ተዝረከረኩ ልሽ። ቆይ ላግዝሽ። ...

**78. SFX: THEY PICK UP THE BOOKS**

***KW END***

**79. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 3: AT POLICE STATION**

**80. ATMO POLICE STATION**

**81. SFX: FOOTSTEPS አቶ ሙላቱ AND OFFICER WALKING**

**82.** አቶ ሙላቱ: ለምን ፖሊስ ጣቢያ እንደምታቆዩኝ ሊገባኝ አልቻለም። እኔ ምንም የሰረኩት ነገር የለም ፖሊስ። ሰዎችን አጠብቃለሁ— ልክ እንደርሶ! መብቶቼን አውቃለሁ።

**83.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(sarcastic)** መብቶች? እዚህ ምንም አይነት መብት የለዎትም አቶ ሙላቱ! አፍዎን ዘግተው ይከተሉኝ።

**84.** አቶ ሙላቱ: **(begs)** እባክዎን ፖሊስ! ባለቤቴን ማናገር አለብኝ ። እንድደውልላት ይፍቀዱልኝ።

**85. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**86.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(sudden change of mood)** በሉ እሺ አቶ ሙላቱ። መበጥበጥ መቼም ይወዳሉ። ዛሬ ግን እድለኛ ነዎት። እዚህ ጠረቤዛ ላይ ያለውን ስልክ ሊጠቀሙ ይችላሉ። በትክክል ሶስት ደቂቃ ነው ያለዎት!። ከዛ በኋላ በዘረፋው ሌላ የማን እጅ እንዳለበት ይነግሩኛል።

***KW BEGIN***

**87.** አቶ ሙላቱ: እኔ እዚህ ውስጥ እጅ የለበትም።

**88.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(cuts in)** እኔ እርስዎን ብሆን ኖሮ ፈጠን ፈጠን እል ነበር። ሁለት ደቂቃ ቀርቶዎታል።

**89.** አቶ ሙላቱ: እኔ--

**90.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(cuts in)** አንድ ደቂቃ ተኩል…

**91.** አቶ ሙላቱ: **(sighs)** እሺ እሺ

***KW END***

**92. SFX: CHAIR BEING PULLED BACK**

**93. SFX: PHONE BEING PICKED UP; DIALLING**

**94.** አቶ ሙላቱ: **(dials)** ዜሮ – አራት – ሶስት – ስምንት – ስድስት – ዜሮ – አምስት **(fade under as we follow the officer)**

**95. SFX: STEPS AS OFFICER STEPS ASIDE**

**96.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(in a low voice)** ፖሊስ!

**97. OFFICER 2:** አቤት መኮንን!

**98.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(in a low voice)** ማን ጋ እንደደወለ እና ምን እንደሚል በዛኛው ስልክ አጣራ።

**99. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 4: አቶ ሙላቱ’S FAMILY IN TANDIKA SLUMS

**100. ATMO: TANDIKA, INSIDE ምህረት’S HUT**

**101. ብሩክ COUGHS THROUGHOUT THE SCENE**

**102. SFX: SCRAPING ON PLATE WITH SPOON**

**103. ቅዱስ:** እማ! ስኳር ድንቹን ትጨምሪልናለሽ?

**104. ወ/ሮ ሉሊት:** አይቻልም ቅዱስ። የቀረው ለእህትህ ምህረት ነው። ከትምህርት ቤት መምጫዋ ደርሷል። (deep breath) አድምጡኝ። እዛ ላቦራያ አክስታችሁ ለምለም ቤት ሳላችሁ ስለሆነው ነገር ሁሉ እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ።

**105. SFX: ወ/ሮ ሉሊት’S MOBILE PHONE RINGING**

**106. ቅዱስ:** አይ እማ እዛ የነበረው እኮ--

**107. ብሩክ:** (cuts in) እረፍ ቅዱስ ስለእዛ ማውራት የለብንም።

**108. ወ/ሮ ሉሊት:** ምንድን ነው? እንዴ  ለኔማ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ።

**109. ብሩክ:** እማዬ ስልክሽ አሁንም እየጮኸ ነው።

**110. ወ/ሮ ሉሊት:** (sighs)

**111. SFX: CELL PHONE BEEPS**

**112. ወ/ሮ ሉሊት:** ሄሎ?

**113.** አቶ ሙላቱ: **(on the phone)** በስንት እዳ ተገኘሽ ሉሊት። ከፖሊስ ጣቢያ ነው የምደውለው ብዙ ላናግርሽ አልችልም።

**114.** ወ/ሮ ሉሊት: እሺ የኔ ውድ፤ ሙላቱ

**115.** ብሩክ: አባዬ ነው የደወለው ላናግረው እፈልጋለሁ።

**116.** ቅዱስ: እኔም!

**117.** ወ/ሮ ሉሊት: **(to the kids)** ልጆች አረፉ! ሂዱ ደጅ ወጥታችሁ ተጫወቱ።

**118.** ቅዱስ/ብሩክ: እሺ እማዬ

**119. SFX: FOOTSTEPS - TWO BOYS LEAVING**

**120.** ወ/ሮ ሉሊት: **(calls after the kids)** በኋላ እናወራለን!

**121.** አቶ ሙላቱ: ሉሊትዬ፤ እንዴት ነሽ? ልጆቹስ ደህና ናቸው?

**122.** ወ/ሮ ሉሊት: ውይ ሙላቱ ከየት ብዬ እንደምጀምርልህ እንኳን አላውቅም። ልጆቹ የቀረችንን ስኳር ድንች ነው አሁን የበሉት።ነገ ምን እንደምሰጣቸው እንኳን አላውቅም። በዛ ላይ እዛ በነበሩበት ጊዜ ስለተፈጠረው ነገር አልነገሩኝም። ብሩክን ያስለዋል– ይህ ደግሞ እያስጨነቀኝ ነው ።

***KW BEGIN***

**123.** አቶ ሙላቱ: የብሩክ ነገር እያሳሰብሽ ይተወዋል። ለምን እህቴን ለምለምን አትደውይላትም? እሷ ትንሽ ገንዘብ ልትልክልሽ ትችላለች።

**124.** ወ/ሮ ሉሊት: **(interrupts him)** የዚህችን ሰው ስም አትጥራብኝ። ለነገሩማ ልጆቻችንን ልትንከባከብ ነበር። ለመሆኑ ራሳቸውን ችለው እዚህ ድረስ እንደመጡ ታውቃለች? ጉዳይዋም አይደል!

**125.** አቶ ሙላቱ: ሉሊት ለማይሆን ኩራት አሁን ጊዜ የለንም። ደውይላት በኋላ--

**126.** ወ/ሮ ሉሊት: **(cuts in)** ያልሞከርኩ መሰለህ? ይቺ ቦቅቧቃ ስልኳን አትመልስም።ገና የምጠይቃት ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ!

***KW END***

**127.** አቶ ሙላቱ: **(sighs, more to himself)** ጥሩ። እኔ በበኩሌ ሌላ ምንም አማራጭአይታየኝም። ... ቆይኝ ሉሊት። መኩሪያን ታውቂዋለሽ አይደል?

**128.** ወ/ሮ ሉሊት: የምክር ቤት አባሉ? በሚገባ አውቀዋለሁ!

**129.** አቶ ሙላቱ: ለምን ስትይ እንዳትጠይቂኝ ግን ሄደሽ ገንዘብ ስጠኝ ካልሽው ይረዳሻል። አደራ ሌላ ጥያቄ እንዳትጠይቂው። ሰምተሸኛል? ባለቤቴ እንደሆንሽ እና እኔ እንደላኩሽ ንገሪው። እሱ ገንዘቡን ይሰጥሻል። አሁን መሄድ አለብኝ።

**130.** ወ/ሮ ሉሊት: ቆይ እንጂ ሙላቱ... ምን ማለትህ ነው? ከመኩሪያ ጋ ሆነህ የአቶ ጃለታን ንብረት ሰርቀሀል እንዴ? እ? ለዛ ነው እሱ ገንዘብ የሚሰጠኝ?ሙላቱ...

**131.** አቶ ሙላቱ: **(angry)** ሴትየ ይህን ሁላ ጥያቄሽን ተይ። እንዳልኩሽ ብቻ አድርጊ።

**132. SFX: LINE DISCONNECTS**

**133.** ወ/ሮ ሉሊት: ሙላቱ, ቆየኝ... ሄሎ! ሄሎ?

## 134. OUTRO - NARRATOR:

**በየቀኑ ለምህረት እናት ለወ/ሮ ሉሊት ህይወት እየከበደች መታለች። ለምን ይሆን ባለቤታቸው አቶ መኩሪያ ዘንድ ባለቤታቸውን የሚልኩት? ልጃቸው ምህረትስ የእርግዝናውን ጉዳይ ምን ታደርግ ይሆን? ይህንን ለማወቅ የበማድመጥ መማርን ቀጣይ የጭውውት ክፍል ይከታተሉ። እስከዚያ ግን** dw.de/lbe**ን ጎብኙ ወይንም በፌስቡክ ገፃችን ላይ ስለ ድራማው ተወያዩ። መልካም ጊዜ!**